# ኮሮና ቫይርስ እና የቆዩ በሽታዎች

## ተጨማሪ የመከላከል መንገድ

ከፍተኛ የደም ግፊት፤ ስኳር፤ አና ሌሎች ለረዥም ጊዜ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ያልሆኑ ተላላፊ በሽታዎች ያሉባቸው አዋቂዎች ለኮሮና ቫይርስ በይበልጥ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ሁላችንም ስርጭቱን የማቆም እንዲሁም ታካሚዎቻችን ከቫይርሱ የመከላከል ሚና መጫወት አለብን።

## ለጤና ባለሙያ የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች



- በጤና ተቋም ውስጥ፤ መደበኛ የሆኑ የብክለት ጥንቃቄ መርሆችን፤ የህክምና ቁሳቁሶችን ከብክለት ነጻ ማድረግን ጨምሮ፤ በሁሉም ታካሚዎች ተግባራዊ ማድረግ።
- ሳል ወይም ጉንፋን መሰል ምልክት ያላቸውን ታካሚዎች በልየታ ክፍል ቀድሞ መለየት እና ማግኘት አስፈላጊ ነው። ከተቻለም ከመደበኛው የታካሚዎች መቆያ ውጭ፤ ከሌላ ታካሚ ጋር ግንኙነት በሌለው መልኩ እንዲቆዩ ማድርግ።



- ከፍተኛ የደም ግፊት፤ ስኳር፤ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታ ያለባቸው ታካሚዎችን በስልክ ደውሎ ወይም በስልክ የጽሁፍ መልክት አማካኝነት የጤና ሁኔታቸውን መከታተል እና የጤና አቅድ ማውጣት።
- የኮሮና ቫይርስ ወረርሽኝ በተከሰተባቸው አካባቢዎች፤ አላስፈላጊ ተጋላጭነትን ለማስቀረት ሲባል፤ ታካሚዎቸ የህመም ምልክት ወይም አጣዳፊ የጤና እክል ካልገጠማቸው በስተቀር ወደ ጤና ተቋም እንዳይመጡ ማበረታታት ።
- ሳል ወይም ጉንፋን መሰል ምልክት ያላቸው ታካሚዎችን፤ የአተነፋፈስ ጥንቃቄ* እንዲጠቀሙ በማድረግ ቫይረሱ ከሰው ወደ ሰው የመተላለፍ እድሉን መግታት ይቻላል።



*https://www.who.int/publications-detail/infection-prevention-and-control-during-health-care-when-novel-coronavirus-(ncov)-infection-is-suspected-20200125

- የጤና ሁኔታቸው የተረጋጋ መሆኑ ለተረጋገጠ ታካሚዎች፤ በተቻለ መጠን ረዘም ላለ ጊዜ የሚሆን መድሃኒት ማዘዝ ( ለ90 ቀን ቢሆን ተመራጭ ነው!)
- ለረዥም ጊዜ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ተላላፊ ያልሆኑ በሽታ ያለባቸው ታካሚዎች፤ በተቻለ መጠን ማህብረሰብ አቀፍ ተንቀሳቃሽ የመድሃኒት መስጫ ወይም መሸጫ ማእከላትን በማዝጋጀት፤ አገልግሎታቸውን ከኮሮና ቫይርስ ህክምና መስጫ ጤና ማእከላት ማራቅ ።

Resolve to Save Lives በሚሊዮን የሚቆጠሩ የልብና የደም ቧንቧ በሽታ ያላባቸው ሰዎችን ከሞተ እና ወረርሽኝ ለመከላከል እየሰራ ነው ። ለተጨማሪ መረጃ ከታች ያለዉን ድህረገፅ ይጎብኙ። www.resolvetosavelives.org and www.preventepidemics.org.

RESOLVE TO SAVE LIVES
AN INITIATIVE OF VITAL STRATEGIES